# የሥራ አጥነት ኢንሹራንስን ከ26 ሣምንታት በላይ ስለማራዘም

የተሻሻለበት ቀን አክቶበር 6 ቀን 2020

የሥራ አጥነት ኢንሹራንስ (UI) ለሠራተኞች የ26 ሣምንታት መነሻ ጥቅማ ጥቅሞችን ለሠራተኞች ያቀርባል፤ ሆኖም ግን ካሣው በሁለት የ13-ሣምንት ማራዘሚያዎች አማካኝነት እስከ አንድ ዓመት ጊዜ ሊራዘም ይችላል፡፡

**የ13-ሣምንት ማራዘሚያዎች አውቶማቲክ አይደሉም! የሥራ አጥነት ኢንሹራንስ ጥያቄ አቅራቢዎች የተራዘመ ድጋፍ ለማግኘት ማመልከት እና ማመልከቻ መሙላት አለባቸው፡፡**

ሁለት የማራዘሚያ ፕሮግራሞች አሉ፡- የወረርሽኝ ድንገተኛ የሥራ አጥነት ካሣ እና የተራዘሙ ጥቅማ ጥቅሞች፡፡ በኮቪድ-19 ድንገተኛ የሕዝብ ጤና ችግር ምክንያት ለሥራ አጥነት ኢንሹራንስ ያመለከቱ ሠራተኞች መጀመሪያ ለPEUC ማመልከት አለባቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት ማራዘሚያዎቹ የወረርሽኝ ሥራ አጥነት እገዛ (ፓንደሚክ አንኢምፕሎይመንት አሲስታንስ) (PUA) ላይ ተፈጻሚነት የላቸውም፤ ይህም በድምሩ ለ39 ሣምንታት ይቆያል፡፡

## የወረርሽኝ ድንገተኛ የሥራ አጥነት ካሣ

**የሥራ አጥነት ኢንሹራንስ ማግኘት የጀመሩት በጁላይ 1 ቀን 2019 ወይም ከዚያ በኋላ ከሆነ እና ለ26 ሣምንታት ጥቅማ ጥቅሞች ሲያገኙ ከቆዩ፣ ለወረርሽኝ ድንገተኛ የሥራ አጥነት ካሣ (PEUC) የ13-ሣምንት ማራዘሚያ ለማግኘት ብቁ ነዎት፡፡**

የመጀመሪያው 26 ጥቅማ ጥቅም የሚያገኙባቸው ሣምንታት ሲገባደዱ ወደ does.dcnetworks.org/initialclaims በመሄድ ለወረርሽኝ ድንገተኛ የሥራ አጥነት ካሣ (PEUC) ያመልክቱ፣ የሚጠይቅዎትንም ይከተሉ፡፡

በሥራ አጥነት ኢንሹራንስ ላይ ባሉበት ጊዜ ገቢዎ ካልተለወጠ በቀር ከሥራ አጥነት ኢንሹራንስ የሚያገኙትን ተመሳሳይ ገንዘብ መጠን በወረርሽኝ ድንገተኛ የሥራ አጥነት ካሣ ያገኛሉ፡፡ እነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች እስከ ዲሴምበር 26 ቀን 2020 ድረስ እስከ 13 ሣምንታት ይገኛሉ፡፡

## የተራዘሙ ጥቅማ ጥቅሞች

**የመጀመሪያዎቹን የ26 ሣምንታት የሥራ አጥነት ኢንሹራንስ ጥቅማ ጥቅሞች እና የ13-ሣምንታት የወረርሽኝ ድንገተኛ የሥራ አጥነት ካሣ (PEUC) ካጠናቀቁ፣ በኤክስቴንድድ ቤኔፊትስ (EB) ፕሮግራም አማካኝነት የ13 ሣምንታት ተጨማሪ ጠቅም ለማግኘት ብቁ ይሆናሉ፡፡**

የወረርሽኝ ድንገተኛ የሥራ አጥነት ካሣ (PEUC) የ13-ሣምንት ማራዘሚያ ሲያበቃ ወደ does.dcnetworks.org/initialclaims በመሄድ ለኤክስቴንድድ ቤኔፊትስ ያመልክቱ፣ የሚጠይቅዎትንም ይከተሉ፡፡

በገቢዎ ላይ ለውጥ ከሌለ በስተቀር በሥራ አጥነት ኢንሹራንስ (UI) እና በወረርሽኝ ድንገተኛ የሥራ አጥነት ካሣ (PEUC) አማካኝነት የሚያገኙትን ተመሳሳይ ሣምንታዊ የገንዘብ መጠን ያገኛሉ፡፡ በዲስትሪክት ኦፍኮሎምቢያ የሥራ አጥነት መጠን ከመደበኛው በላይ ሆኖ እስከቀጠለ ድረስ ኤክስቴንድድ ቤኔፊትስ ይኖራል፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡-** elissasilverman.com/ui_extendedbenefits

esilverman@dccouncil.us • 202-724-7772
@CM_Silverman CMElissaSilverman

DC COUNCIL AT-LARGE
Elissa
★★★ SILVERMAN